

# የጀግና ልጅ ጀግና እንጂ የእሳት ልጅ አመድ አይሆንም



ለጠላት መንበርከክ ለባዕዳን ዓለም
ታሪክን መለወጥ በሰው ሰራሽ ቀለም
አሳልፎ መስጠት ብሄራዊ ጥቅም
ወገንን መበደል በጥላቻ በቂም
በፍፁም!! የህዝባችን ባህል አልነበረም።

**ዛሬ ተፈጠረ ከሃዲ ውዥንብር**
**ሀገሩን እንደ ዕቃ የሚቸረችር**
**አፓርታይድ ስርዓት አፍኖ የሚያስር**
**ትግራይ ጉድ ወለደች በደደቢት ምድር።**

**የዮሐንስ ሀገር የራስ አሉላ**
**ዛሬ ትግራይ ጉግ ማንጉግ አብቅላ**
**የሰላም ፀር እሾኽ አሜኬላ**
**ወገን አጣች የሚሆን ከለላ**
**የሞተላት ሳይሆን የገደላት በላ።**

መይሳው ዮሐንስ በታሪክ ሲዘከር
አንገቱን የሰጠ ለሀገሩ ክብር
በአጥንቱ ያጠረ ዳር ድንበር
በደሙ የፃፈ የታሪክ ማሕደር።
ዛሬ በባዕድ ተደፈረ
ፍትሕ በሐሰት ተቀየረ
የወላጅ አደራ ተሰበረ
ወገን ታጣ የጠነከረ
<u>የተጋሩ ሱሪ ከአሉላ ጋር አብሮ ተቀበረ።</u>

የጀግኖች አገር የራስ አሉላ
ዛሬ ትግራይ ጉግ ማንጉግ አብቅላ
የሰላም ፀር እሾኽ አሜኬላ
እናቱን የሚሸጥ የባዕድ ደላላ
የሳህል ምንደኛ የውጭ ዲቃላ
በአውራጃ በዘር ተከፋፍላ
ወገን አጣች የሚሆን ከለላ
<u>የሞተላት ሳይሆን የገደላት በላ።</u>

ያደግንበት ያገራችን ምድር
የወገን እትብት ያባቶች መቃብር
አንበሳ ተኝቶ ዝንጀሮ ሲጨፍር
ነፃነት ተነጥቆ ህዝቡ ሲቸገር
ጎሮሮ ተዘግቶ መውጫ መጊቢያ በር
<u>እናት ሀገራችን ሽባ ሆና ስትቀር።</u>

እውነት!! ደደቢት የትግራይ ህዝብ ልደት?
ወይስ የሀገር ገመና የክሕደት
የጨለማ ቀን የደም ሰንበት
የውርደት በዓል የወገን ባርነት
ጥቁር ታሪክ የትውልድ ሀፍረት።

ወገኖቼ!! እስቲ ለሃቅ ለእውነት ፍረዱ
እነ አረጋዊ ገ/ዮሐንስ የት ሄዱ?
ስንት ሰው ደማ ስንቶቹ ታረዱ
ስንት ሰው ታጎረ ስንቶቹ ተሰደዱ
እነስክንደር አንዱላም ወህኒ ሲወርዱ
አስፋልቶች በንፁኃን ደም ሲለበዱ
ማን ይበል አቤት ያልቆመ ለሆዱ?

ሽፍታ በህዝብ ላይ ሲቀልድ
ወገን ታጣ ፈጥኖ ደራሽ ዘመድ
ፍርሃት ነገሰ ተኰላሸ ትውልድ
<u>የእሳት ልጅ ጠፋ ሁሉም ሆነ አመድ።</u>

እነ አቶ ሽብሩ እነ አቦዬ አይነጋ
የባዕድ ወኪል የከሃዲ መንጋ
በጥቂት ማፍያ ሀገር ሲናጋ
ዓይናችን እያየ በራችን ሲዘጋ
**በቁም እንቅልፋችን ስንዘናጋ**
**<u>ጆሯችን ቆርጠው ሲሰጡን ስጋ።</u>**

ታዲያ!! ይኼው ነው ልማቱ ድግሱ?
ከደደቢት ከጥዋቱ ከጥንሱሱ
የካቲት አሃዱ ብለው ሲነሱ
በማር ጠቅልለው መርዝ ሲያጎርሱ
ባህላችን በርዘው ታሪክ ሲያራክሱ
ሉዓላዊ ክብር ሀገር ሲያፈርሱ።

**አዎ!! ለጠላት መንበርከክ ለባዕዳን ዓለም**
**ታሪክን መለወጥ በሰው ሰራሽ ቀለም**
**በፍፁም!! የህዝባችን ባህል አልነበረም።**

አባ ታጠቅ መይሳው ካሳ
እምዬ የሐንስ የማይረሳ
የታሪክ አሻራ የድል አንበሳ
ምን ይል ነበር? ዛሬ ከመቃብር ቢነሳ?

**ጥቂት ተጋሩ የባዕዳን ባንዳ**
**ለእኩይ አላማ ለሕቡእ አጀንዳ**
**ሳህል ተጠንስሳ ደደቢት ተወልዳ**
**ዛሬ ትግራይ ተሸከመች መከራና ዕዳ**
**<u>መቋጫ የሌለው የዘመናት ፍዳ።</u>**

ማን ይሁን ከሳሽ ማን ይሁን ዳኛ
በገዛ ሀገሩ ሆኖ ጥግኛ
በገዛ መሬቱ ሆኖ ጢሰኛ
በገዛ መብቱ ሆኖ ምፅዋተኛ
የበይ ተመልካች ሆኖ ተስፈኛ
ወኔው ተሰልቦ ሲሆን ሞርኰኛ
<u>ውሸማ ይገባል ባለቤት ሲተኛ።</u>

የቀውጥ ቀን ፈጥኖ ደራሽ
ወገን ታጣ የሚሰጥ ምላሽ
ልጅ ጠፋ ጀግንነት ወራሽ
<u>ለሆዱ አደረ ለፍርፋሪ ቁራሽ።</u>

የጅብ ገበሬ የአህያ በሬ
የዝንጀሮ ጎልጓይ ጦጣ ዘር አቀባይ
ሀገር አጥፊ ፀረ ልማት ዓባይ
አንድም የሌላቸው ሁሉም እንብላ እንብላ ባይ

ይገርማል!! የናት ሆድ ዥንጉርጉር
አንዱ ለሀገሩ ሌላው ለወንበሩ
አንዱ ለህዝቡ ሌላው ለገንዘቡ
አንዱ ለሃቅ ሌላው ለስርቅ
አንዱ ለእውነት ሌላው ለውሸት
አንዱ እየለማ ሌላው እየተጠማ
በሐሰት ምስክር ታጎሮ በመጨለማ
እናት ልጇ ስትል ለብሳ ጥቁር ሸማ
አድማጭ ታጣ ረዳት የሚሰማ
ወላድ መኻን ሆነች እማማ እማማ።

በሀገርም በውጭም ያላችሁ
መልእክቴን አድምጡኝ እባካችሁ እባካችሁ!

**አንተ!!** የለውጥ ሞተር ተማሪ መምህሩ
ወጣት ሽማግሌ ገበሬ ላባደሩ
ሙስሊም ክርስቲያን መስጊዱ አድባሩ
ደራሲ ሙዚቀኛ ኪነት መዘምሩ
ሰዓሊ ጋዜጠኛ መሳሪያው ብዕሩ
ሀገር ወዳድ ዜጎች ሁሉም በድምሩ
ለወገን ጥብቅና ካልጮኹ ካልተነጋገሩ
<u>ምንድን ነው ትርጉሙ በዚች ዓለም መኖሩ?</u>

ሁሉም ካልተነሳ ካልተባበረ
ከእንቅልፉ ካልነቃ ካልጠነከረ
የሰደድ በሽታ ፍርሃት ካልሰበረ
ሌላ የለም አማራጭ ቁምነገር
እርዳታ የሚሰጥ ነፃነት የሚቸር
መፍትሔው እኛው ነን ስንተባበር
ወፍ ዘራሽ ሳንሆን በቁም ሳንቀበር
ብለን እንነሳ ቀልድ የለም በሀገር።

ከበላይ ገሰሰ